# “የፍርድ በትር፤ በማናለብኝነት ንፁሀን ላይ የሚለጠፍ መርግ አይደለም”

ከቴዲ አፍሮ ጉዳይ ጊዜያዊ ኮሚቴ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ
16 December 2008

ስለ ፍትህ፣ ስለ ፍቅርና መቻቻል በማቀንቀኑ ምክንያት በህግ ሽፋን እየተፈፀመበት ያለውን በደል ተከትሎ ፤ “ የፐርዥያ የንጋት ወፍ በመባል ከምትታወቀው ከማርዘይህ፣ ከግሪኳ መሉና ሜርኩሪና ከብሪታኒያዋ ቫኔሳ ሬዴግሬቭ ተርታ ሊሰለፍ ይገባዋል” የሚል ምስክርነት የተሰጠለት ኢትዮጵያዊው ድንቅ አርቲስት ወጣት ቴዎዴሮስ ካሳሁን ፤ ባሳለፍነው ሳምንት በተከሰሰበት ጉዳይ የ6 ዓመት እስራትና የ 18 ሽህ ብር ቅጣት እንደተጣለበት ለሁላችንም ግልፅ ነው።

ይህንኑ ተከትሎ በአገር ቤትም ሆነ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሀዘናቸውንና ቁጣቸውን በተለያዩ መንገዶች ያለማቋረጥ እየገለፁ ሲሆን ፤ በመላው ዓለም ህዝባዊ ተቃውሞውን በተቀናጀ መልኩ የሚያስተባብር 25 አባላት ያሉት ጊዜያዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ የተጠናከረ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በሰሜን አሜሪካ በሚገኙ ስቴቶችና በአብዛኞቹ የአውሮፓ አገራት የሚኖሩት የኮሚቴው አባላት ዲሴምበር 18 ቀን 2008 ዓ፣ም ባካሄዱት አስቸኳይ ስብሰባም፤ የፊታችን ጃንዋሪ 14 ቀን 2009 ዓ፣ም በመላው ዓለም ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ እንዲጠራ ውሳኔ ላይ ደርሰው ለተግባራዊነቱ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ሊይ ይገኛሉ።

ዕውቅ የህግ ባለሙያዎች የተካተቱበት ይህ ኮሚቴ ፤ለተቃውሞ ሰልፉ ከሚያዘጋጃቸውና ለሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ ለመንግስታትና ለተለያዩ አህጉራዊ ተቋማት ከሚያቀርባቸው ሰነዶች መካከል፤ የቴዲ አፍሮ የክስ ሂደት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ማለትም ከከሳሽ የሰነድ ማስረጃ አቀራረብ ጀምሮ እስከ ፍርድ ድረስ የነበረው ሂደት ስህተት እንደሆነና በአገሪቱ ህግ ሳይቀር ቴዲ በነፃ መሰናበት የነበረበት መሆኑን፣ በህግ ሽፋን በወጣቱ ከያኒ ላይ የተፈፀመው በደል፤ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ላይ በየዕለቱ እየተፈፀሙ ያሉት አገራዊ ወንጀሎች ቅጥያ መሆኑን የሚያመለክቱ ሰነድች ይገኙበታል። ምርጫ 97ትን ተከትሎ በቅንጅት ደጋፊነት ወህኒ ከተወረወሩት ውስጥ እስካሁን በየእስር ቤቱ እየማቀቁ የሚገኙ ወገኖችን ስም ዝርዝር ለሚመለከታቸው አካላት ማስተላለፍ እና ከመቼውም ጊዜ በላይ በመላው አገሪቱ በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ በስፋት የሚፈፀመውን እስር፣ ውክቢያና ዛቻ በተብራራ መልኩ ማሳወቅም ሌላው የኮሚቴው ተግባር ነው።

እንዲሁም፤ ዓለማቀፉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች የሆነው ሂዩማን ራይትስ ዎች በተጨባጭ ማስረጃ ይፋ እንዳደረገው፤ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የሚደረገው ፍፁም ጭካኔ የተመላበት ጭፍጨፋ ፤ ሰልፈኞች ለወገኖቻቸው ድምፃቸውን ከሚያሰሙባቸው አጀንዳዎች አንዱ ነው።

ውድ ኢትዮጵያውያን፣ ኮሚቴው፤ ማንም ሰው ከህግ በላይ እንዳልሆነ አበክሮ ያምናል። ቴዎዴሮስ ካሳሁን ያለምንም ቅዴመ ሁኔታ በነፃ መለቀቅ አለበት የሚል ድምፁን የሚያሰማውም፤ ቴዎዴሮስ ታዋቂ ሰው ስለሆነ ጥፋት ቢያጠፋም ሊታለፍ ይገባዋል ከሚል

ውሀ ከማይቋጥር መከራከሪያ በመነሳት አይደለም።ይልቁንም መነሻችን ከላይ እንደተገለፀው፤ ቴዎዴሮስ ካሳሁን ወንጀል ስለመፈፀሙ በዓቃቤ ህግ የቀረበው የተሣሳተ ምናልባትም " ሆን ተብል የተፈበረከ" ማስረጃ ነው። ሆኖም፤ የቴዲን በነፃ መለቀቅ የምንጠይቀው፦ " አንድ ንፁህ ሰው በተሣሳተ ማስረጃ ከሚቀጣ፤ መቶ ወንጀለኞች በነፃ ቢለቀቁ ይሻላል" በሚለው የህግ ሰዎች አባባል ስላትም አይደለም።ይህን አባባል እኛ አገር ባለው የጨለመ ሁኔታ ማንሳት፤ ቅንጦት ይሆናል። እኛ የምንለው፦ "ቴዲ በማያሻማ ሁኔታ ነፃ መሆኑ ስለተረጋገጠ ፤ነፃ መለቀቅ አለበት" ነው።

እኛ የምንለው፦ "የፍርዴ በትር፤በማናለብኝነት በንፁህን ላይ የሚለጠፍ መርግ አይደለም" ነው።

የፍቅር ሰባኪና የሰላም አምባሳደራችን በሆነው ቴዎዴሮስ ካሳሁን ላይ ፤ ህግን ሽፋን ለማድረግ በመሞከር በማናለብኝነት እንደመርግ የተለጠፈው የፍርድ በትር፤ ከ80 ሚሊዮን በሚበልጠው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተፈፀመ አገራዊ ወንጀል ነው የሚል ፅኑ እምነት የያዘው ጊዜያዊ ኮሚቴያችን፤ በኢትዮጵያ ፤ህግ ንፁህንንና ደካማዎችን ማጥቂያ መሳሪያ እንዱሁም፤ ፖሉስም፣ ዓቃቤ ህግም፣ ዳኛም፣ ህግም አንድ ሰው ብቻ ከሆነ እና ፍትህ ጨርሶ ከምድሪቱ ከጠፋ ዓመታት መቆጠራቸውን ይገነዘባል። ስለዚህም ፤ያለማቋረጥ የሚፈሰው የሚሉዮኖች ዕምባ እስኪታበስ ድረስ ዓለማቀፍ ጥረቱን አጠናክሮ ይቀጥላል። በዚህም መሰረት፤ በመጨው ጃንዋሪ 14 ቀን 2009 ዓ.ም. በዓለማቀፍ ደረጃ በተጠራው ተቃውሞ ላይ፤ በአሜሪካ የተለያዩ ስቴቶች እና በአውሮፓ የተለያዩ ከተሞች የምትኖሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤ በተለያዩ ሚዲያና በየከተሞቻችሁ ባሉት የኮሚቴው አባላት አማካይነት በሚደርሳችሁ ፕሮግራምና ጥሪ መሰረት ወደ ተቃውሞ ሰልፉ በመውጣት፤ ወገናዊና አገራዊ ድምፃችሁን ታሰሙ ዘንድ ከወዲሁ በአክብሮት እናስታውቃለን።

*ለበለጠ መረጃ አቶ ታማኝ በየነን በ hawarya@gmail.com ወይንም ክንፉ አሰፋን በ kinfuassefa@gmail.com ማነጋገር ትችላላችሁ።*

የቴዲ አፍሮ ጉዳይ ጊዜያዊ ኮሚቴ